# ለኮሌራ ወረርሽኝና ሌሎች የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች እየተሰጠ ያለውን የጤና ምላሽ አስመልክቶ የተዘጋጀ ሳምንታዊ መግለጫ ሰኔ 11/2011

• በአጠቃላይ በሀገራችን በኮሌራ ወረርሽኝ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 614 ደርሷል።

• በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሀረርጌ ዞን በጭሮ ወረዳ 74፣ በኦዳ ቡልቱም ወረዳ 128፣ በሜኤሶ ወረዳ 34፣ ገመቺስ ወረዳ 9 እንዲሁም በበዴሳ ከተማ 42 በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በሰንዳፋ ከተማ 6 ሰው እንዲሁም በበራክ ወረዳ 1 ሰው በአጠቃላይ 294 ሰዎች በበሽታው የተያዙ ሲሆን እስካሁን የሁለት ሰዎች ህይወት በበሽታው ምክንያት አልፏል፤

• በአዲስ አበባ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ 22 ሰው፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ 17 ሰው፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ 6 ሰው፣ በልደታ ክፍለ ከተማ ሰው 5 ሰው፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ 1 ሰው፣ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ 8 ሰው፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ 2 ሰው፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ 1 እንዲሁም በአራዳ ክፍለ ከተማ 6 ሰው በአጠቃላይ 70 ሰዎች የበሽታው ምልክት ታይቶባቸው ህክምና ተደርጎላቸው ወደ መደበኛ ህይወታቸው ተመልሰዋል። በአዲስ አበባ በለይቶ ማቆያ የተኛ ተካሚ የለም ።

• በድሬዳዋ አስተዳደር አንድ ሰው በበሽታው ተይዟል ውጤቱም በላብራቶሪ ተመርምሮ ቪብሮ ኮሌሬ መሆኑ ተረጋግጧል።

• በአማራ ክልል በዋግህምራ ዞን አበርገሌ ወረዳ 82 ፣ በሰሜን ጎንደር ዞን ጠለምት ወረዳ 112፣ በበየዳ ወረዳ 3 እንዲሁም በአዊ ዞን ዳንጓ ወረዳ 1 በአጠቃላይ 198 ሰዎች በበሽታው የተያዙ ሲሆን እስከ አሁን ድረስ የ14 ሰዎች ህይወት በበሽታው ምክንያት አልፏል፣

• በሶማሌ ክልል ቦክሎማዮ ወረዳ 33 ሰዎች የአተት ወረርሽኝ ምልክት ታይቶባቸው ታክመው ወደመደበኛ ስራቸው ተመልሰዋል።

• በትግራይ ክልል በምስራቃዊ ዞን ክልተአውላዕሎ ወረዳ፣አድግራት ከተማ፣ እንዲሁም በመቀለ ዙሪያ ሰሜን ክፍለ ከተማና አዲሃቂ ክፍለ ከተማ በአጠቃላይ 18 ሰዎች በበሽታው ተይዘዋል።

• ወረርሽኙ በተከሰተባቸው ክልሎች በበሽታው የተያዙ ሰዎችን ለይቶ ለማከም የሚያስችሉ በአጠቃላይ 18 ለይቶ የማከሚያ ማዕከላት የተቋቋመ ሲሆን እነዚህም በኦሮሚያ ስድስት ማዕከላት ተቋቁሟል ( በኦዳቡልቱም 1፣ በጪሮ 4 ፣በሰንዳፋ ከተማ 1 እና በሜኤሶ 3)፣ በአዲስ አበባ ሁለት ( ድል ፍሬ 1ና አዲስ ከተማ 1)፣ በትግራይ ክልል አንድ ( በመቀሌ አዲሃቂ 1) እንዲሁም በአማራ ክልል ስድስት ( አበርጌሌ ወረዳ 3፣ አባይ ማዶ ህርዳ 1 እና ጠለምት 2) ናቸው።

• ወረርሽኙ በተከሰተባቸው ክልሎች ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች የመለየት ስራ ተከናውኗል በዚህም መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ተቋማት የፌደራል ማራሚያ ቤቶች ፣ የአረጋዊያንና የአእምሮ ህሙማን ማገገሚያ ማእከላት፣ የጎዳና ህፃናት ማገገሚያ ማእከላትና የአዳሪ ት/ቤቶችን እንዲሁም በዚህ ስራ ላይ ብቻ ለተሰማሩ የጤና ባለሙያዎች በአጠቃላይ ከ17 ሺህ በላይ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ክትባቱ በሁለት ዙር የሚሰጥ ሲሆን የመጀመሪየው ዙር ከነገ ጀምሮ የሚሰጥ ይሆናል። ከዚህም ጋር በተያያዘ ተቋማት እንዲተባበሩና ለመከተብ ዝግጁ እንዲሆኑ ኢንስቲትዩቱ ይጠይቃል።

• በሽታውን በቶሎ ለመቆጣጠር የበሽታዎችን መንስኤ በጥናት በመለየትና ናሙናዎችን በላብራቶሪ በማረጋገጥ ለሁሉም ክልሎች መድሀኒቶችና የህክምና ግብአቶች ወደ ህክምና ጣቢያዎች እንዲከማቹ ተደርጓል።

• ከኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ምክርቤት(መጅሊስ) ጋር የኮሌራ በሽታ መከላከል ስለሚቻልባቸው መንገዶችን በተለይም የእምነቱ ተከታዬች ማድረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ ውይይት ተደርጓል። በመጅሊሱ በኩል በየመስጊዱ በጎ ፈቃደኞችን መድበው እንደሚሰሩ መግባባት ላይ ተደርሷል። እንዲሁም ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር ውይይት ተካሄዶ በት/ት ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም እንዲጀመር ስምምነት ላይ ተደርሷል።

የኢቦላ ወረርሽኝና ሌሎች የህበረተሰብ አደጋዎችን በተመለከተ

• የኢቦላ ቫይረስ ወረርሽኝ በአህጉራችን አፈሪካ በአሁን ወቅት በሁለት ሀገራት ማለትም በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎና በዩጋዳ የሚገኝ ሲሆን በተለይም በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎና ከ 2014 ጀምሮ የተከሰተ ሲሆን በአሁን ወቅት በሰሜን ኪቩ ፕሮቪንስ ወረርሽኙ ተቀስቅሶ የብዙ ሰዎችን ህይወት እየቀጠፈ ይገኛል። በባለፈው ሳምንት ውስጥ በዩጋንዳ 3 ሰዎች በቫይረሱ የተየያዙ ሲሆን ከበሽታው ጋር በተያይዞ የ3 ሰዎች ህይወት አልፏል። ወረርሽኙ የተከሰተው በዲሞክራቲክ ቲፐብሊክ ኮንጎ አዋሳኝ በሆነ አከባቢ ነው። ይሁንና ዩጋንዳ ወረርሽኙ ከመከሰቱ በፊት በአከባቢው ለሚሰሩ ጤና ባለሙያዎች ክትባቱን የሰጠች ሲሆን ሌሎች የምላሽ መስጠት ስራዎችን በማከናወን ላይ ትገኛለች።

• በኬኒያ በኬሪቾ ካውኒቲ አንድ ሰው በኢቦላ ቫይረስ በሽታ የተጠረጠረ ሲሆን ውጤቱም ኔጌቲቭ መሆኑ ተረጋግጧል ይሁንና ጉዳዩን በጥብቅ እየተከታተለነው እንገኛለን።

• ወረርሽኙ ወደ ሀገራችን እንዳይገባ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እያከናወንን እንገኛለን። በዚህም

o በቦሌ አለም አቀፍ የአውሮፕላን ጣቢያ የተጓዠችን የሙቀት መጠን የልየታ ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

o በአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢየውም በበሽታው የተያዙ መንገደኞች ቢያጋጥሙ ለይቶ ለማከም የሚያስችል ቦታ ተዘጋጅቷል ከዚህም በተጨማሪ በቦሌ ጨፌ የኢቦላ ለይቶ ማከሚያ ማዕከል ተዘጋጅቷል። ህክምናውን መስጠት የሚችሉ ባለሙያዎችም በተለያዩ ጊዚያት እየሰለጠኑ ይገኛሉ

o በሌላ መልኩ ከዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ወደ ሀገራችን ለሚገቡ መንገደኞች ከገቡበት እለት ጀምሮ ለ21ቀናት ባረፉበት ቦታዎች የህክምና ክትትል እየተደረገ ይገኛል ። ከሜይ 8፣2018 ጀምሮ ከ15 ሺህ በላይ ከዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የመጡ መንገደኞች ላይ የልየታ ስራ የተከናወነ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 1882 መንገደኞች ላይ ለ21 ቀናት ክትትል ተደርጓል፣ በአሁን ወቅት 214 መንገደኞች ባረፉበት ቦታ ሆነው ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል።

• የችኩንጉኒያ ወረርሽኝ በሶማሌ ክልል ቀብሪ ዳሃር ከተማ 115 ሰዎች ላይ ተከስቷል። በተጨማሪም በአከባቢው ከሚገኘው የመከላከያ ካምፕ 25 ታማሚዎች መኖራቸው ተረጋግጧል። በአጠቃላይ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር 140 ነው።

o ወረርሽኙን ለመቆጣጠር እንዲቻል በአከባቢው ለበሽታው መስፋፋት አጋላጭ የሆኑ ቦታዎች የመድሃኒት ርጭት መካሄድ ጀምሯል። ይሁንና ማንኛውም በበሽታው የተያዘ ሰው በቶሎ ወደ ህክምና ተቋም በመሄድ የህክምና አገልግሎት ማግኘት የሚችል ሲሆን በተጨማሪም ማህበረሰቡ እራሱን ከበሽታው ለመከላከል አጎበር እንዲጠቀም እንዲሁም ለትንኞች መራቢያ አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን እንዲያስወግድ ኢንስቲትዩቱ በድጋሚ ያሳስባል።

• የወባ በሽታ በወረርሽኝ መልክ በአሁን ወቅት በሀገራችን በተለያዩ ክልሎች የታየ ሲሆን በተለይም በደቡብ ክልል በወላይታ ዞን በ 6 ወረዳዎች (በዳሞት ጋሌ፣ በቦሌሶሬ፣ በቦሎሶ ቦምቤ፣ ኪንዶ ኮይሻ፣ ዳሞቴ ሶሬ እና ዳጉና ፉነጎ) እንዲሁም በአማራ ክልል በባህርዳር ዙሪያና ደራ ወረዳዎች ተከስቷል። ህብረተሰቡ የትንኝ መራቢያ አመቺ የሆኑ የታቆሩ ውሃዎችን በማፋሰስ እንዲሁም የአልጋ አጎበር በመጠቀም እራሱን ከወባ ትንኝ ንክሻ እንዲከላከል እናሳስባለን።

• የኩፍኝ በሽታ በአፋር ክልል በአሳይታ ወረዳ የተከሰተ ሲሆን በወረርሽኙ 256 ሰዎች ተይዘዋል። ይሁንና ወረርሽኙን አስቀድሞ ለመከላከል እንዲቻል ክትባት በወረዳው ተሰጥቷል። በአሁን ወቅት 26 የሚሆኑ ህሙማን በአሳይታ ሆስፒታል ህክምና እየተደረገላቸው ይገኛል።
• የጊኒዎርም በሽታ በጋምቤላ ክልል በጎግ ወረዳ በ4 ዝንጅሮዎች ላይ የተገኘ በመሆኑ ኢኒስቲትዩቱ ከእንስሳት ወደ ሰው እንዳይተላለፍ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ሲሆን ከዚህም ጋር በተያያዘ በአከባቢው የሚገኙ ማህበረስቦች ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል።

በመጨረሻም፡-

• ከክረምቱ ጋር ተያይዞ በተለይም በጎርፍ ምክንያት ውሃዎች መበከል ሊያጋጥማቸው ይችላል በመሆኑም ህብረተሰቡ ለመጠጥ የሚጠቀመውን ውሃ በውሃ ማከሚያ ኬሚካሎች በማከም ወይም አፍልቶ እንዲጠቀም እናሳስባለን።
• ወቅቱ የዝናብ ወቅት በመሆኑ ለወባ ትንኝ መራባት አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር ስለሆነ ህብረተሰቡ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ እንመክራለን።

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
ሰኔ 11 / 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ